# አቡ ሩሚ[1] ለመጀመሪያ ጊዜ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማርኛ የመለሰ ኢትዮጵያዊ ሊቅ

ቅዱሳት መጻሕፍት ኦሪት እና መጻሕፍተ ብሉይ እና አዲስ ከዕብራይስጥ እና ከጽርዕ ከአረብም በቀጥታ ወደ ግዕዝ ተተርጉመው ሲሰበክባቻው እና ትምህርት ሲሰጥባቸው መቆየታቸውን ረጂሙ ታሪካቸው በሰፊው በየቦታው ተዘግቦ ይገኛል። መጽሀፍ ቅዱስ እንዳለ ወደ አማርኛ የተመለሰበት ጊዜ ግን በጣም ቅርብ ነው። የግዕዙ ትርጉም ካስራምስት መቶ ዘመን በላይ ሲያስቆጥር ያማርኛው ከሁለት ምዕት አያልፍም። ያም ሆነ ይህ ይህን ታላቅ ስራ ማለት መጽሐፍ ቅዱስን ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ አማርኛ የመለሰው አቡ ሩሚ ወይም አባ አብርሀም እንደሆነ ታሪኩን የዘገበው እንግሊዛዊ ቄስ ዊሊያም ጆዌት *ክርስቲያናዊ ምርምር በሜዲትራኒያን*[2] በሚለው መጽሐፉ በሰፊው አብራርቶታል። በዚህ በተጠቀሰው መጽሀፍ ውስጥ ቄስ ጆዌት ፷ገጽ ሙሉ ስለ ኢትዮጵያ (በዚያን ጊዜ አቢሲኒያ) ብቻ ይተርካል። ታሪኩንም ለማስታወስ ያህል እንደሚከተለው በድርሞ ቀርቧል።

ቄስ ዊሊያም ጆዌት እንደ አመተ እግዚእ በ፲፰፻፳ዓ/ም ካይሮን ሲጎበኝ በጊዜው የፈረንሳይ ቆንሲላ የነበረውን አስሊንን ያገኘዋል። አስሊን ይህ በአብርሀም የጅ ጽሁፍ የተተረጎመው መጽሐፍ ቅዱስ በጁ ይገኝ ነበር። አስሊን ለጆዌት ሲያጫውተው አንድ ከጎንደር የመጣ ሽማግሌ ዕድሜው ፲ ወይም ፲፭ ገደማ የሚሆነው ሰው እንዳገኘ ስሙም አቡ ሩሚ(አብርሀም) የሚባል ለጀምስ ብሩስ አስተርጓሚ በነበረበት ጊዜ ገና የ፳፪ አመት ጎልማሳ እንደነበር ይገልጽለታል። ባገኘው ጊዜ በጣም ታሞ እንደነበር እና ቤቱ እንዳስጠጋው ያወጋዋል። በቤቱም የምግብ የመኝታ እና የህክምና አገልግሎት በተጨማሪ የጽህፈት መሳሪያዎችን ያቀርብለት ነበር። አስሊን የዚህን ኢትዮጵያዊ ዕውቀትና ችሎታ ካስተዋለ በኋላ መጽሐፍ ቅዱስን እንዳለ ወደ አማርኛ እንዲተረጉምለት ያግባባዋል። እንዴት እንደተረጎሙትም አስሊን ዝርዝሩን እንደሚከተለው ያብራራል።

ይህ የትርጉም ስራ ፲ አመት ፈጅቶበታል (1808-1818) አስሊን ስለ ትርጉሙ ስራ ሲተርክ ሁልጊዜ ማክሰኞ እና ቅዳሜ በሩ ለእንግዶች ተዘግቶ እያንዳንዱን አረፍተ ነገር ከፍ ባለ ጥንቃቄ ቀስ እያለ ከሚተረጉት ያረብኛ ቅጅ ያነባል። ላረብኛው እንግዳ እና አስቸጋሪ ፍች የማይገኝለት ከሆነ ከሮሜው፣ ከሶሪያው ቅጅ እና ራሱ ከሰበሰባቸው ሙዳየ ቃላትና አስተያየቶች ጋር ያመሳክራል። ብዙን ጊዜ አስቸጋሪውን ቃል ከግዕዙ መክፈቻ ያገኝ እንደነበረ አስሊን ያስረዳል። በተጨማሪም አንዱን መጽሐፍ ሲጨርሱ የጨረሱትን በደንብ በገጽ በገጹ ሳይደራጁ እና ሳያቀናጁ ሌላ አዲስ እንደማጀምሩም በመግለጽ የትርጉሙን ስራ በዚህ ዓይነት መጨረሳቸውን ያወሳል።

አስሊን ይህን በጁ የሚገኘውም የአብርሀምን የአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ የጅ ጽሁፍ ትርጉም ወጪውን የሚሸፍንለት ከሆነ ለመሸጥ ሀሳቡ ነበረው። በዚያን ጊዜ ስራቸው መጽሐፍ ቅዱስን በየቋንቋው መመለስ የሆነው የእንግሊዝ የውጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር እና የቤተ ክርስቲያን የመልዕክተኛ ማህበር ትልቅ ፍላጎት እንዳላቸው አስሊን ተገንዝቧል። በመጨረሻ ይህ ማህበር ጉዳዩን ለቄስ ጆዌት ይሰጠዋል። ጆዌትም ጉዳዩን ከዳር ያደርሳል ማለት በክፍያ ያጠናቅቀዋል። ይህም ዋጋው £1250.00 ይከፈላል ይህ ከዛሬ ፪፻.አመት በፊት እጅግ ብዙ ገንዘብ ነው።

ይህ ጆዌት የገዛው ያብርሀም የጅ ጽሁፍ ፱ሺ.ህ ፳፻፴፱ገጽ ያለው ሲሆን ለዕርማት ተብሎ ለፕ/ር ሳሙኤል[3] እና ለቶማስ ፕላት[4] ተሰጥቶ እነሱም ለዕትመት አዘጋጅተውት ወንጌሉ እንደ አመተ እግዚእ በ፲፰፻፳፬ ዓ/ም ሲታተም አዲስ ኪዳን ደሞ ፲፰፻፳፱ዓ/ም መታተሙን ሙሉው መጽሐፍ ቅዱስ ደሞ ፲፰፻፵ መታተሙን ፕ/ር ኡልንዶርፍ *ኢትዮጵያ እና መጽሐፍ ቅዱስ*[5] በሚለው መጽሐፋቸው ጠቅሰውት ይገኛል። ከዚህ በኋላ በተለያየ ጊዜ እና የተለያዩ ዕትመቶች ትንሽ እየለዋወጡ እንደወጡ ይታወቃል። የትኛው ገዳም እንደሆነ አልተጠቀስም እንጂ ኦርጂናሌው የአቡ ሩሚ ያማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ በ፲፰፻፰ዎቹ እንደተገኘ ይነገራል። ፕ/ር ኡልንዶርፍ እንዳሉት "አጼ ኃ/ሥ አዲስ ትርጉም እንዲዘጋጅ አዘው እስከወጣበት ጊዜ እስከ ፲፱፻፰ ድረስ ያቡ ሩሚ ቅጂ ከትንሽ ለውጥ እና ማሻሻያ ጋር ከዚም ከዚያም እያለ ቆይቷል"[6]

አባ አብርሀም የተወለደው እ.አ.እ. ፲፯፻፷፪ አካባቢ በጎንደር ሲሆን ቄስ ይሁን መነኩሴ የታወቀ ነገር የለም ምንም የታወቀ የቤተ ክህነት ሹመት የለውም። ትምህርቱ ግን ያው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እንደሆነ ይታወቃል። አገሩን ሲለቅ የ፳፰አመት ጎልማሳ እንደነበር እና ካይሮን፣ እየሩሳሌምን፣ ሶሪያን ካየ በኋላ በአርመን እና በኢራን በኩል አርጎ ወደ ህንድ እንደ ተጓዘ ታሪኩ ተመዝግቧል። ህንድም በዊሊያም ጆንስ[7] ቤት እንዳረፈ አማርኛና ግዕዝ ያስተምረው እንደነበር አስሊን ይገልጻል። ለትንሽ ጊዜ ውድ አገሩን አይቶ እንደገና ወደ ካይሮ ተመልሶ በነበረበት ጊዜ ነው አስሊን ያገኘው። የትርጉሙን ስራ ካጠናቀቀ በኋላ እየሩሳሌምን ለሁለተኛ ጊዜ ከጎበኘ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ካይሮን በጊዜው አጥቅቷት በነበረው ወረርሽኝ ተይዞ በ፲፰፻፲፱ዓ/ም ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል።

*ያገራችንን ታላታቅ ሰዎች አገሬው አያውቃቸውም እንዲታወቁ የምታውቁ ሰዎች ብታሳውቁ የታሪክን አደራ ከመወጣታችሁም በላይ በዚህ በኩል ያለውን ያገሪቷን ትግል ማገዝ ነው። ያገራችንም ታላላቆች ለዝንት ዓለም እንዲዘከሩ ማድረግ የሊቃውንት ድርሻ ነው።*

ክንፈ ሚካኤል
*መጋቢት ፪ቀን ፳፻፩ ዓ/ም*
ሜልበርን

[1] የተለያየ መጠሪያ እዳለው ፕ/ር ኤድዋርድ ኡልዶርፍ ኢትዮጵያና መጽሐፍ ቅዱስ በሚለው መጽሐፋቸው ገልጸውታል። አቢ. ሩሀ፣ አባ ሩካህ ሃቢሲነስ (ባረብኛ አብርሀም ማለት እንደሆነም ይገልጻሉ)

[2] Jowett, W, 1824 Christian Researches in the Mediterranean. London

[3] በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲ ያረብኛ እና የዕብራይስጥ መምህር የነበረ

[4] የእንግሊዝና የውጭ የመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር የቤተ መጻሕፍት አቃቤ የነበረ

[5] Ullendorff, Edward, 1968. Ethiopa and the Bible, Oxford: The British Academy

[6] ዝኒ ከማሁ

[7] የታወቀ የሰነ ፍጥረት ሊቅ እንደሆነ ፕ/ር ኡልንዶርፍ ከላይ በተጠቀሰው መጽሐፋቸው ገልጸውታል